# «ጴጥሮስ ያቺን» ቃል!

መክብብ ማሞ (mekbma@yahoo.com)

**«ፋሺስቶች ያገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢሉዋቸው እውነት እንዳይመስላችሁ:: ሽፍታ ማለት ያለ አገሩ መጥቶ የሰውን አገር የሚወር ይህ በመካከላችሁ መጥቶ የቆመ አረመኔው የኢጣሊያ ፋሺስት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው:: የኢትዮጵያ መሬት እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን::» አቡነ ጴጥሮስ::**

*ያለፈው ረቡዕ ሐምሌ 22 ቀን ጀግናው ሰማዕት አቡነ ጴጥሮስ በግፍ የተገደሉበት 73ኛ ዓመት ነበር:: እኒህ ታላቅ አባት ለሰማዕትነት ያበቃቸው ዋናው ምክንያት በወቅቱ ለተጠየቁት ቀላል ለሚመስል ጥያቄ «ቃሌን አልክድም» ብለው በመቆማቸው ነበር::*

*ፋሺስት ኢጣሊያ አገራችንን ወርሮ ሕዝቡን ባስጨነቀ ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ ከአርበኛው ጋር በመቆም የጣሊያንን ሠራዊት በድፍረት ሲቃወሙና አርበኛውንም ሲደግፉ ቆይተዋል:: ሆኖም ከጊዜያት በኋላ በፋሺስቶች ቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ጣሊያኖች ራሳቸው በሰየሚቸው ዳኞች ፊት አቡኑን ለፍርድ በማቅረብ ከላይ ሲታይ በጣም ቀላል የሚመስል ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል:: የጥያቄው ዓላማ አቡኑን የጣሊያን ተገዢ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ የነበረውን ሕዝባዊ ዓመጽ ለማብረድ ቢቻልም ደግሞ የብዙሃኑን ድጋፍ ለማግኘት የታሰበበት ነበር::*

*ስለዚህም የግራዚያኒ ዳኞች አቡነ ጴጥሮስን ለፍርድ ባቀረቧቸው ጊዜ የጠየቋቸው - «ሊቀጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ እንዲሁም ሌሎች የጣሊያንን የበላይነት ተቀብለዋል:: እርስዎም እንዲሁ ተቀብለው ሌሎችም እንዲቀበሉ ቢያደርጉ ይሻላል - ብቻዎን ማመጽ ምንም አይሰራልዎትም:: ይህንን ቢያደርጉ ምን ይመስልዎታል. . . » የሚል አንደምታ ነበረው:: አቡኑም «ሕዝቡ እንዳይፈጅ. . . መከራው እንዲቀል - ሕጻናቱና አዛውንቱ እንዲሁም ሴቶች እንዳያልቁ . . » የሚል ምክንያት በመደርደር «ከመሞት መሰንበት» በማለት የቀረበላቸውን ምክር አዘል አስተያየት መቀበል አላቃታቸውም:: ሆኖም ለእምነታቸውና ለሕዝባቸው የገቡትን ቃል ከሚክዱ ሞትን እንደሚመርጡ በድፍረት ለዳኞቹ መለሱላቸው - እንዲህም አሉ «አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ናቸው ፣ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም:: እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ . . . ስለ አገሬና ስለ ቤተክርስቲያኔ እቆረቆራለሁ:: . . . እኔን ለመግደል እንደወሰናችሁ አውቃለሁ:: በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ» የሚል ነበር::* **(ጳውሎስ ኞኞ፤ «የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት»፣ አአ 1980)**

*ረቡዕ ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓም* (July 29, 1936) *አቡነ ጴጥሮስ ከፊት ለፊታቸው የተደገነውን የጣሊያንን መትረየስ ሳይፈሩ ከመገደላቸው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሚከተለውን በመናገር የመጨረሻ ቃላቸው ሰጡ - ለቃላቸውም እስከ ሕልፈተ ሕይወታቸው ድረስ በታማኝነት ቆሙ:- «ፋሺስቶች ያገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢሉዋቸው እውነት እንዳይመስላችሁ:: ሽፍታ ማለት ያለ አገሩ መጥቶ የሰውን አገር የሚወር ይህ በመካከላችሁ መጥቶ የቆመ አረመኔው የኢጣሊያ ፋሺስት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው:: የኢትዮጵያ መሬት እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን::»* **(ጳውሎስ ኞኞ፤ «የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት» አ.አ. 1980፣ ገጽ 157)**

*የፋሺስት የጦር መኮንኖችና ጄኔራሎች በተሰበሰቡበት አደባባይ ከዚህ በኋላ የተሰማው የማያቋርጥ የጥይት እሩምታ ነበር:: ከመስቀል በቀር ሌላ «መሳሪያ» በእጁ የሌለ የአንድ ሃይማኖት አባት «ቃል» የግራዚያኒን ጦር ወኔ ሰለበው:: ለአቡኑ አንድ ጥይት አልበቃ ብሏቸው የእሩምታ ተኩስ በመልቀቅ በግፍ ረሸኗቸው::*

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ሰባት ዓስርተ ዓመታት ቆይቶ አሁን ባለንበት ዘመንም ይህ «ቃልን» የመካድ ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡ ተጠያቂዋ ጴጥሮስ አምጦ የወለዳት የ«ቃል» ልጁ ብርቱካን ነበረች፡፡ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ቀላል የሚመስል ጥያቄ ነበር የተጠየቀችው፡፡ «ሌላ አሳዳጊ ወላጅ የሌላትን አንዷን ልጄን ለማን ጥዬ?» «ሟሪ የሌላትን እናቴንስ ለማን ትቼ?»፣ «በብዙ ድካምና ውጣውረድ የመሰረትነውን አንድነትን ለማን አስረክቤ. . . ?» የሚሉ አሳማኝ የሚመስሉ ጥያቄዎችን በመደርደር የተጠየቀችውን ማስተባበያ መስጠት ትችል ነበር፡፡

ሆኖም የመጨረሻዋ የቁርጥ ሰዓት በደረሰች ጊዜ በግፍ እና በማንአለብኝነት የከሰሷት «ቃልሺን ስጪ» ብለው ባስጨነቋት ጊዜ የዕድሜ ልክ እስራት ፊቷ ተደቅኖ ያስፈራራት በነበረው ቀውጢ ጊዜ «ቃሌማ እንደ አባቴ ነው» በማለት የማያወላውል መልሷን በድፍረት ሰጠቻቸው፡፡ ለሃቅ መቆሟን፣ ሃላፊነት ለሰጣት ሕዝብ ታማኝ መሆኗን አረጋገጠች፡፡ «እኔ ሃላፊነት ያለብኝ የሕዝባዊ ፓርቲ መሪ ነኝ፡፡ ስለ ሃገሬ፣ ስለ ሕዝቤና ስለፓርቲዬ እቆረቆራለሁ፡፡ ከዚህ በቀር እናንተ ለጠየቃችሁኝ ማስተባበያ የምሰጠው ቃሌን ነው፡፡ ሌላ ምንም የማቀርበው የለኝም፡፡ ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ» በማለት የጀግናውን ሰማዕት ቃል ደገመችው ፣ ከሰባት ዓስርተ ዓመታት በኋላም ሕያው አደረገችው፡፡

ግሪካዊው ፈላስፋ Diogenes የአቴንስን መንገዶች መኖሪያው ያደረገ ፣ መልካምነትን በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የተረጎመ የሶቅራጥስ ደቀመዝሙር ነበር፡፡ ይህ ፈላስፋ ከጎዳና ተዳዳሪነት ሌላ ዕድሜውን በትልቅ ማሰሮ ውስጥ በማሳለፍ ማኅበራዊ እኩልነትን ከመስበክ አልፎ በተግባር እንደኖረው ታሪክ ያወሳል፡፡ ከሁሉ በላይ የሚታወቅበት ዋንኛው ተግባሩ ግን በቀን ኩራዝ አብርቶ ይዞር የነበረ ሲሆን ይህንን ያደርግ የነበረው ለቃሉ የቆመ ሃቀኛ ሰው ፍለጋ እንደሆነ ይነገርለታል፡፡

ከሦስት ዓሥርተ ዓመታት በፊት ባገራችን ኢትዮጵያ የሃቅ እና የቃል ነገር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነበር፡፡ «ኃይለሥላሴ ይሙት» ብሎ ቃሉን የሰጠ ሰው የፈለገ ነገር ቢሆን ቃሉን እንደማያጥፍ ታማኝነቱ ሲገልጽ ቃል ተቀባዩም የቃሉን እውነታነት ተቀብሎ ማድረግ የሚገባውን በእምነት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ቃላባይነት በማኅበረሰቡ ዘንድ እጅግ የተወገዘ ተግባር ስለነበርም «የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ» የሚለው አባባል ሰዎች ምን ያህል ለቃላቸው ታማኝ እንደነበሩ በግልጽ የሚያስረዳ እውነታ ሆኖ ቆይቷል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን እንኳን በቃል ይቅርና በጽሁፍ የተረጋገጠ ፣ በዕማኝ የተመሰከረ ፣ በማኅተም የጸና (ምናልባትም በድጋይ የተጠረበ) ምንም ነገር የማይከበርበት ዘመን ላይ እንገኛለን፡፡ ከቤተመንግሥት እስከ ቤተክህነት ድረስ በሃላፊነት ላይ የሚገኙ ሁሉ ከዚህ በኋላ የሚመጣ ሌላ ትውልድ የሌለ ይመስል ፣ ቢኖርም ምንም ሊተርፈው የሚገባ ነገር እንዳይኖር እልህ የተጋቡ ይመስል የሃገርን ሃብት አለገደብ ሲዘርፉ ይገኛሉ፡፡ አገር የማስተዳደሩን ኃላፊነት በሕጋዊም ሆነ በሕገወጥ መንገድ ይዘውት የሚገኙ «ሲሾም ያልበላ . . . » የሚለውን አባባል እውነተኛነት ሳታረጋግጡ ከስልጣን እንዳትለቁ የተባሉ ይመስል የሃገርንና የሕዝብን ሃብት መዝረፋን ከተያያዙት ሃያ ዓመት ሊሞላቸው ምንም አልቀረውም፡፡ በሃይማኖት ድርጅቶች አካባቢ የሚገኙ የዕምነት መሪዎች ምዕመኖቻቸውን ለሃቅ ፣ ለእውነት መቆምን ከማስተማር ይልቅ «የባሰ አታምጣ አርፋችሁ ተገዙ» በማለት ራሳቸው ቃላባይ ሆነው ምዕመኖቻቸውም እንዲሁ እንዲሆኑ በቃልና በተግባር እየሰበኩ ይገኛሉ፡፡ ታዲያ በዚህ ዘመን እንኳን በኩራዝ በፓውዛም ተፈልጎ ለቃሉ የሚቆም ሰው መታጣቱ ምን ይደንቃል? አንዲት ብትገኝ እርሷኑም አጠፏት፡፡

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

በስፖርተኛታቸው እና ቁጥብ የህይወት መመሪያ ተከታይነታቸው የሚታወቁት የራሺያው ጠቅላይ ሚኒስትር ቭላዲሚር ፑቲን አገራቸውን በፕሬዚዳንትነት በመሩባቸው ዓመታት ውስጥ በራሺያ የሰካራም ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንደቀነሰ በአንድ ወቅት ቢቢሲ ሲዘግብ ሰምቼ ነበር፡፡ (ከፑቲን በፊት የነበሩትና በመጠጥ አዘውታሪነታቸው የሚታወቁት ፕሬዚዳንት ቦሪስ ዬልሲን እንደነበሩ እዚህ ላይ ልብ ይሏል፡፡) ወደ አገራችን ስንመጣ ለዓመታት ከመጠን በላይ እየጨመረ የመጣ ነገር ቢኖር የጫት ቃሚ ቁጥር መብዛት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሙስና፡፡ ለችግሩ መፍትሔ የተገኘ ይመስል እንዲያውም የሙስናው ጉዳይ መስሪያቤት እስከማቋቋም አድርሷል፡፡

የተዘነጋው ትልቁ ነገር ግን መልካምንም ይሁን መጥፎን ነገር ሕዝብ ከመሪው የሚማር መሆኑን ነው፡፡ እንደ አቡነ ጴጥሮስ እስከሞት ለቃሉ ታማኝ በመሆን በተግባር የሚያስተምረውን መሪም ሆነ የሃይማኖት አባት ሕዝቡ ይሻል፡፡ ይህንን ደግሞ ከቤተመንግሥትም ሆነ ከቤተክህነት ይጠብቃል፡፡ እንደዚህ ታማኝ የሆኑ መሪዎች ከሁለቱም ቦታ ካልተገኙ አሁን ላሉት መሪዎች «አልገዛም» በማለት የአቡኑን «ቃል» መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ ግዝት እንዳለብን አንዘንጋ - ያውም እንዲህ የሚል «የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው፡፡» ታዲያ ለዚህ ውግዘት የምንሰጠው ምላሽ ምንድርነው? የምንመልሰውስ «ቃል» ምን ይሆን? የጴጥሮስን ያቺን ቃል?

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com